Dmujids Volume 6 Issue II 2022 DOI: 10.20372/dmujids 1000

# በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፤የአብነት ትምህርት ቤት ተግዳሮቶች በደብረማርቆስ ከተማና በጎዛምን ወረዳ ተተኳሪነት፤

*Tarik Ejigu*[1]*, *Alemakef Tenager*[1]

[1]Ethiopian Language and Literature Amharic, Social Science and Humanities, Debre Markos University, Debremarkos, Ethiopia

*Corresponding author Email: ejigutarik@gmail.com , tarik_ejigu@dmu.edu.et

## አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ በደብረማርቆስ እና ጎዛምና ወረዳ አካባቢ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስተያን በአብነት ትምህርት ቤት የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች መመርመር ነው። አላማውን ለማሳካት አይነታዊ የጥናት ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን፣ ውስን የጥናት ስልት ተግባራዊ ተደርጓል፡ ፡ አላማ ተኮር የንሞና አመራረጥ ስልትን በመጠቀም የጥናቱ ተሳታፊዎችና ቦታዎች ተመርጠዋል። በዚህም መሰረት መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም ከሀገረስብከቱ ሀላፊዎችና ከምእመኑ ተመርጠዉ ቃለ መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት አድርገዋል። በተመረጡ ገዳመ አስቄጠስ ትክለሃይማኖት አንድነት ገዳም (የቅኔ)፤እንድማጣ ግነተ እየሱስ (የቅኔ)፣ መንበረ ስብሃት ቅድስት ስላሴ ( የቅኔና የአቋቋም)፤ግምጃ ቤት ኪዳነምህረት(አጫብር)፤ጥሑመልሳን ወይንማ ማርያም (የዜማ)፤ የዛንግራ ቅዱስ ሚካኤል (የዜማ) ፤የደረባን ቅዱስ ሚካኤል (የዜማ) እና ሌሎች የአብነት ትምህርት ቤቶች ላይ አንድ አንድ የቡድን ተኮር ዉይይት እና ምልከታ ተደርጓል። ካልአይ የመረጃ ምንጮችም ለቀዳማይ መረጃ ምንጮች ማመሳከሪያነት አገልግለዋል። በእነዚህ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚያሳዩት በደብረማርቆስ እና ጎዛምና ወረዳ አካባቢ ያሉ የአብነት ትምህርት ቤቶች ለመዳከም ምክንያቶች መሰረታዊ ፍላጎቶች አለመሟላት፣የአብነት ተማሪዎች የተሻለ የስራ አማራጭ መፈለግ፣የጤና ችግሮች መኖር እና የዘመናዊ ትምህርት ፍላጎት በወላጆችና በተማሪዎች እየጨመረ መምጣት ትልቅ ምክንያት ሆኗል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚታየው የአብነት ትምህርት ቤቶች በመዳከማቸው ምክንያት በሀገርም ሆነ በማህበረሰቡ ላይ የተጋረጡ ተግዳሮቶች አሉ። እነሱም የአብያተ ክርስቲያን ቁጥር ባለበት መቆም ይህ የሆነው የምእመኑ ቁጥር እየጨመረ ቢመጣም በምእመኑ ልክ ቤተክርስቲያናት አለመገንባታቸው ነው የሚያሳየው። ለዚህ ምክንያቱ አገልጋይ ካህናትና ዲያቆናትን ማፍራት አለመቻሉ፤ሌላው በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ቅርሶች መጥፋት፤ ከትምህርቱ የጊዜ እርዝማኔ የተነሳ ተማሪ የሌላቸው የትምህርት አይነቶች መጨመር፤ ምእመኑ ሃይማኖታዊ አገልግሎቶች (ቅዳሴ፣ክርስትና፣ፍትሃት፣ንስሃ እና ሌሎችንም አለማግኘት በዋናነት የተስተዋሉ ጉዳዮች ናቸው። ከዚህ አንጻር የአብነት ትምህርት ቤት የትውልዱን ስነምግባር ከመገንባት እና ብቁ ዜጋ ከማፍራት አንጻር አስተዋጽኦ አለው። ስለዚህ ተቋሙ*

*ተጠናክሮ እንዲቀጥል ቤተክህነቱ፣ የመንግስት አስተዳደር አካላት፣ ማህበረሰቡ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ባለሀብቶች ሃላፊነታቸውን ቢወጡ የሚሉት ምክረ-ሀሳቦች ተቀምጠዋል፡፡*

**ቁልፍ *ቃላት*፡-** *ኦርቶዶክስ-ተዋህዶ፣አብነት-ትምህርት፣ተማሪዎች፣መምህራን*

# 1. *መግቢያ*

## 1.1. *የጥናቱ ዳራ*

*ኢትዮጵያ የተለያየ ባህል፣ትውፊትና ሃይማኖት ባለቤት የሆነች ሃገር ናት፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና እምነት ተከታይ የሆነው የማህበረሰብ ክፍል መንፈሳዊና ባህላዊ ቅርሶች አሉት፡፡ መሸሻ* (2011) *የሃይማኖቱ ተከታይ ህዝብ የማንነት መገለጫ የሆነው ትልቁ ተቋም የአብነት ትምህርት ቤት*[1] *ነው። በመሆኑም* Enbakom (974;12) *እንደገለጸው፡- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የአብነት ትምህርት ቤት፤ በቤተ-እምነቱ ከሚስተዋሉት ተቋማት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህ የትምህርት መስክ ለብዙ አመታት ዘመናዊ ትምህርት ባልነበረበት ወቅት በብቸኝነት በቤተክህነት አካባቢ ይሰጥ የነበረ ትምህርት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በዚህ መንፈሳዊ ተቋም በርካታ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ የሆኑ የአብነት ተማሪዎች የእውቀት ባለቤት ከማድረጉ ባሻገር በአለማዊውም ጭምር የእለት ከእለት የህይወት ማሳለጫ በመሆን ያገለግል ነበር፡፡ በመሆኑም፤ በወቅቱ በቤተ-ክህነትም ሆነ በቤተ-መንግስት ይሰጥ የነበረው አገልግሎት በአብነት ትምህርት ቤት ተምረው ባለፉ ሊቃውንት ነው፡፡ ስለዚህ ትምህርቱ ለሃገር እድገትና ግንባታ፤ለሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት መጎልበት ከፍተኛ የሆነ አገልግሎት ይሰጥ የነበረ ትምህርት ነው፡፡ ከዚህ ባህሪው የተነሳ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚሰጠው የአብነት ትምህርት ቤት የሚሰጡ ትምህርቶች* Mezmur (2011). *በአብነት ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሚማሯቸው የትምህርት አይነቶች ንባብ ቤት፣ቅዳሴ ቤት፣ዜማ ቤት፣ቅኔ ቤት፣ አቋቋም ቤት፣ መጽሀፍ ቤት…እየተባሉ ይከፋፈላሉ፡፡ እነዚህ ትምህርቶች ትውፊታዊ ከመሆናቸው በተጨማሪ የዕውቀት መሠረት ናቸው፡፡*

*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አብነት ትምህርቶች በርካታ ጥቅሞች እንዳሏቸው* Hilegebrel (1994;13) *ሲገልጽ፡- የአብነት ትምህርት ቤቶች ማንበብና መፃፍን ለሰዎች በማዳረስ ረገድ፣የሂሳብ፣ የስነጥበብ፣ የመድሃኒት፣ የህግና አስተዳደርና ክህሎት ግንባታ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ ይህን ሀሳብ በማጠናከር መርሻ* (2011፣6) *ኢትዮጵያ ከስልጣኔዋ ብዛት የተነሳ ስእሎችን፣ ቅርጾችን፣ ሃውልቶችን፣*

[1] የጥናቱ ርእስ የአብነት ትምህርት ቤት ሲል በትምህርት ቤቱ ውስጥ ያሉትን ተማሪዎችና መምህራን የሚያጠቃልል ነው።

ዜማዎችን፣ ፍልስፍና፣ ሂሳብ፣ ለጉሮሮ የተስማማ ለጆሮ የማይጎረብጥ የፊደል ቅርጽ፣ወዘተ.ባለቤት ነች በማለት ያብራራሉ። ስለዚህ የአብነት ትምህርት የሰዎችን እውቀትና ስብዕና ልማት ውስጥ ትልቅ ሚና ከመጫወቱ በተጨማሪ ለእምነቱ ተከታዮች ይህን መንፈሳዊ ሀብት ከትውልድ ወደ ትውልድ በማስተላለፍ ከፍተኛ ሚና ተወቷል። በአጠቃላይ በዚህ የትምህርት ተቋም ያልተነካ የህይወት ክፍል የለም።

የአብነት ትምህርት ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ለሀገር ያበረከተው አስተዋጽኦ ሰዎችን ማልማት ላይ ነው። ይህን በተመለከተ ገነት (ዓመተ ምህረቱ ያልተጠቀሰ) የኢትዮጵያ አብያተክርስቲያን በአብነት ትምህርት ቤት ዉስጥ አባቶች ከማፍራት ባለፈ በአለምአቀፍና በሀገርአቀፍ ደረጃ እንዲሁም በልዩ ልዩ መንግስታዊ ተቋማት የሚያገለግሉ ምሁራን ስታወጣ ኖራለች። ይህን ሃሳብ በማጠናከር Aweke (2015) የአብነት ትምህርት የሀይማኖት መምህራንን ከማስተማር ባለፈ ሌሎች የህዝብ አገልጋዮችን ማለትም ዳኞችን፣ መምህራንን፣ አስተዳዳሪዎችን፣ እንዲሁም መሪዎችንና አምባሳደሮችን በማፍራት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሃዶ የአብነት ትምህርት የራሱን አስቷዋጽኦ አበርክቷል። ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው በኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋሀዶ ሀይማኖት ውስጥ የሚሰጠው የአብነት ትምህርት ዘመናዊ ትምህርት ሳይኖር ቤተክርስቲያኗ ከበርካታ አመታት በፊት ቀለም አዘጋጅታ፤ብራና ፍቃ፤ፊደል ቀርጻ የራሷን እውቀት በራሷ መምህር አስተምራለች። በርካታ ተማሪዎችን የመንፈሳዊና አለማዊ እውቀት ባለቤት አድርጋ በመቅረጽ ለበርካታ አመታት ተግባሯን ስታከናውን ቆይታለች። በተጨማሪ በየትኛውም ዘርፍ የሰው ሃብት ልማት ላይ ከፍተኛ ስራ በመስራት ለሀገር ባለውለታ ናት።

የአብነት ትምህርት ለሀገር በርካታ ውለታዎችን የከፈለና እየከፈለ ቢሆንም የተለያዩ ተግዳሮቶች እየተከሰቱ መምጣታቸው ከላይ የተጠቀሱትን ሀብቶች ሁሉ እያሳጡን ይገኛሉ። በአብነት ትምህርት ቤት ላይ ተግዳሮቶች በተለያየ መንገድ መከሰት የጀመሩት በተለይ ባህሩ (1999) እንደገለጸው፡- ከ20ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የዘመናዊ ትምህርት ጽንሰ ሃሳብ ከተከሰተ በኋላ የአብነት ትምህርቱ ተዳክሟል። ለዚህ እንደምክንያት የሚጠቀሰው ወላጆች ልጆቻቸውን ወደዘመናዊ ትምህርት ቤት ማስገባታቸው ነው። ከዚህ ሃሳብ ጋር በተያያዘ Mezmur (2011,1) የዘመናዊ ትምህርት መስፋፋትን ተከትሎ እነዚህ አገራዊ የእዉቀትና የጥበብ ምንጭ የሆኑት የአብነት ትምህርት ቤት እዉቀቶች እየተረሱ መሄዳቸው ለትምህርት ቤቶች መዳከም እንደምክንያት የሚጠቀስ ሆኗል።

Mezmur (2011,2) ከንጉሳዊው የፖለቲካ ለውጥ ጋር ተያይዞ የመጣው የደርግ ስርአት በኦርቶዶስ ተዋሃዶ ሃይማኖትና በአብነት ትምህርት ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽኖ ማሳደሩ ለችግሩ መጠን መስፋት ምክንያት ሆኗል በማለት ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪ የአብነት ትምህርት ቤቶች ወቅታዊ ሁኔታ ሲቃኝ ፍሬ ከማፍራት ይልቅ በርካታ የአብነት ትምህርት ቤቶች ዝግ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ በመዳከም ላይ እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ የአብነት ተማሪዎች ከቤተክርስቲያን ህይወት በመውጣት ወደዘመናዊው ሲያጋድሉ ይስተዋላል፡፡ ለዚህም Mezmur (2011,3) የአብነት ተማሪዎች በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ትምህርታቸውን እየተዉ ዘመናዊውን ህይወት በመከተል ወደከተሞች በመፍለስ ናቸው በማለት ይገልጻል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ሃሳቦች የምንረዳው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የአብነት ትምህርት ቤት ዘመናዊ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ለሀገር ግንባታ ያበረከተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያ በተለያዩ የመንግስት አገዛዝ ስርዓት ውስጥ ስታልፍ ከስርዓቱ ጋር በተያያዘ የሚከሰቱት ሁነቶች የአብነት ትምህርት ቤት ላይ አሉታዊ ተጽኖዎች ሲያደርሱ ቆይተዋል፤አሁንም እያደረሱ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም በርካታ የአብነት ትምህርት ቤቶች በቁጥር ከመቀነሳቸው በተጨማሪ ትምህርት ቤቱ የሚያፈራቸው ደቀ-መዝሙሮች እና አስተማሪ ሊቃውንት ጭምር ቁጥራቸው ከጊዜ ጊዜ እየሳሳ መሄዱ ለአብነት ትምህርት ቤቱ ትልቅ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ በተጨማሪ በርካታ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አገልግሎት በሚሰጡ አካላት እጥረት ምክንያት ዝግ ሆነዋል፡፡ በሌላ በኩል ለሀገር እድገት ወሳኝ የሆነውን የሰው ሃብት ልማት፤በእውቀት የታነጸ፤ በራሱ የሚተማመን፤ በስነምግባር የታነጸ ትውልድ በመገንባት ረገድ ክፍተቶች ተበራክተዋል፡፡ እነዚህ ተግዳሮቶችን መነሻ በማድረግ በምስራቅ ጎጃም ዞን በጎዛምን ወረዳና በደብረማርቆስ ከተማ አካባቢ የሚገኙ የአብነት ትምህርት ቤቶችን ይዳስሳል፡፡

### 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

ኢትዮጵያ የራሷ የሆኑ ሀገር በቀል እውቀቶች፣ አፈታሪኮችና ሀይማኖታዊ ትምህርቶች ባለቤት መሆኗ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጅ እነዚህን ሃብቶች ጠብቆ ለትውልድ በማስተላለፍ በኩል የነበሩ ችግሮችን ሙህራና እንዲህ ይገልጹታል፡- Munjeri (2000). በርካታ ሰዎች ሀብታቸውን ጠብቀው ለትዉልድ ማስተላለፍ ያለዉን ጥቅም በዉል ባለመረዳት፤ የራሳቸዉን ባህል እንደ ኋላቀር በመቁጠር፣ እንዲሁም በኢኮኖሚ ለማደግ ካላቸው ፍላጎት የተነሳ የአብነት

**ትምህርትን ማነቆ አድርገው የሚቆጥሩ እንዳሉ ያስረዳሉ፡፡ ይህን ሃሳብ በመደገፍ** Jangawe, (2007.1-8.) **ኢትዮጵያውያን በራሳቸው ሚተማመኑባቸው ሀይማኖታዊ እውቀቶች ያሏቸው ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች እየተዳከሙ መምጣታቸውን ያሰረዳሉ፡፡ በተጨማሪ ካለፉት ዘመናት አንጻር በመጠን ደረጃ ሲታይ ወደ አብነት ትምህርት ቤት የሚሄደው ተማሪ ቁጥር እጅግ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ በምልከታ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም የምሁራኑን ሃሳብ እና ምልከታውን በማቀናጀት የዘመናዊነት እሳቤ መስፋፋቱ እና የአብነት ትምህርት ቤት ዋጋ ማጣቱ ምክንያቱ ምን ይሆን? የሚል ጥያቄ መነሳቱ ወደጥናቱ ለመግባት አነሳሽ ምክንያት ሆኗል፡፡**

**ሌላው የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ኢትዮጵያ የራሷ ማንነት እና ሃይማኖታዊ ትምህርት ያላት ሃገር ናት፡፡ በዚህ ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው የአብነት ትምህርት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ብዙ ተመራማሪዎች በጉዳዩ ጥናትና ምርምር አድርገዋል፡፡ ለምሳሌ፡-** Mezmur Tsegaye (2011) "Traditional Education of the Ethiopian Orthodox Church and Its Potential for Tourism Development (1975-present) **በሚል ርዕሰ ጉዳይ ባጠናዉ ጥናት በአገራዊ ባህልና እሴት የተቃኙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ትምህርቶች በትክክል ቢሰራባቸዉ ከፍተኛ የቱሪዝም መስህብ እንደሚሆኑ በጥናቱ አመላክቷል፡፡** Ayenachew (2017) The Ethiopian Traditional Education: Philosophical foundations and reformist movements in Medieval Period. **በሚል ርእስ ባጠናው ጥናቱ እንዳመለከተዉ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ዉስጥ የተነሱትን የነደቂቀ እስጢፋኖስ አስተምህሮ ያጣነዉ እድል በማለት ለማቅረብ ሞክሯል፡፡** Chaillot, (2002). The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church Traditional Brief Introduction to its Life and Spirituality- **በሚለዉ ጥናቷ በከፍተኛ ደረጃ እየተዳከመ የመጣዉ የግዕዝ ቋንቋ ትምህርት በተመለከተ አብራርታለች፡፡**

Ashenafi, (2011):- Ye’kolo-temari: Children’s Perspectives on Education, Mobility, Social Life and Livelihood in the Ethiopian Orthodox Church (EOC) Traditional School in Dangila. **በሚል ርዕሰ የተጠናው ጥናት ትኩረት፤ ተማሪዎች ወደ አብነት ትምህርት ቤቶች እንዲገቡ የሚያደርጋቸዉን ዋና ዋና ገፊ ምክንያቶች በመዘርዘር የተማሪዎችን የቀን ተቀን የህይወት ጉዞ፤የገቢ ምንጫቸዉን እና ማኅበራዊ መስተጋብራቸዉን በመዘርዘር ተተንትኗል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ተመራማሪዎች ትኩረታቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሰጠው የአብነት ትምህርት ለሀገር የቱሪዚም እድገት፣ማህበራዊ መስተጋብር፣**

የቅዱሳኑ አስተምህሮ እና ለሀገር እድገት ያበረከተው አስተዋጽኦ ላይ ነው፡፡
ነገር ግን በተደረገው ዳሰሳ የአብነት ትምህርት ተግዳሮቶችን በደብረማርቆስ ከተማ እና በጎዛምን ወረዳ ለማየት የሞከረ አጥኚ አልተገኘም፡፡ ይልቁንም በመምህራን እና በደቀ መዛሙርት ላይ ሊኖር የሚችለው ተግዳሮት የማጥናት ጉዳይ የተረሳና ያልተዳሰሰ ርዕሰ ጉዳይ ስለሆነ ይህ ጥናት ቢጠና የሚስተዋለውን ክፍተት ይሞላል ተብሎ ይታመናል፡፡

### 1.3. የጥናቱ አላማዎች

ይህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ እና ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

#### 1.3.1. አጠቃላይ ዓላማ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ በደብረማርቆስ እና ጎዛምና ወረዳ አካባቢ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስተያን የአብነት ትምህርት ቤት የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች መመርመር፡፡

#### 1.3.2. ዝርዝር አላማዎች

- በደብረማርቆስ እና ጎዛምና ወረዳ አካባቢ ያሉ የአብነት ትምህርት ቤቶች ለመዳከም ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ መለየት፡፡
- በደብረማርቆስ እና ጎዛምና ወረዳ አካባቢ የሚገኙ የአብነት ትምህርት ቤቶች በመዳከማቸው ምክንያት የተጋረጡ ተግዳሮቶች መጠቆም፡፡

#### 1.3.3. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

- በደብረማርቆስ እና ጎዛምና ወረዳ አካባቢ ያሉ የአብነት ትምህርት ቤቶች ለመዳከም ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?፡፡
- በደብረማርቆስ እና ጎዛምና ወረዳ አካባቢ ያሉ የአብነት ትምህርት ቤቶች በመዳከማቸው ምክንያት የተጋረጡ ተግዳሮቶች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?፡፡

### 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በምስራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት በደብረማርቆስና ጎዛምን ወረዳ አካባቢ በሚገኙ የተመረጡ ገዳመ አስቄጠስ ትክለሃይማኖት አንድነት ገዳም (የቅኔ)፤ እንድማጣ ግነተ እየሱስ (የቅኔ)፣መንበረ ስብሃት ቅድስት ስላሴ (የቅኔና የአቋቋም)፤ ግምጃ ቤት ኪዳነምህረት(አጫብር) ፤ ጥኡመልሳን ወይንማ ማርያም (የዜማ)፤ የዛንግራ ቅዱስ ሚካኤል (የዜማ) ፤የደረባን ቅዱስ ሚካኤል (የዜማ) እና ሌሎች ጥንታውያን የአብነት ትምህርት ቤቶች ላይ የተወሰነ ነዉ፡፡ በይዘት ደረጃም እነዚህ የአብነት ትምህርት ቤቶች ለመዳከማቸው ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ መለየት እና በመዳከማቸው ምክንያት የተጋረጡ ተግዳሮቶችን በመጠቆም እና በመዳሰስ የተወሰነ ነዉ፡፡

### 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ (Significances of the study)

የዚህ ጥናቱ ውጤት የሚከተሉትን ጥቅሞች ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡

1. በደብረማርቆስ እና ጎዛምና ወረዳ አካባቢ ያሉ የአብነት ትምህርት ቤቶች ለመዳከም ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ ለደብረማርቆስ ሀገረስብከት፣

ለአብነት ትምህርት ክፍል መምሪያ መረጃ በመስጠት ያገለግላል ።

2. ዉጤታማነቱ ያልተረጋገጠን ዘመናዊ ትምህርት በጭፍን ከመማር ይልቅ ማህበረሰቡ ወደራሱ እንዲመለከት ሊጠቅመው ይችላል።

3. ለሀገራችን ፖሊሲ አዉጭዎች በአብነት ትምህርት ቤቶች ላይ እየተከሰተ ያለውን ተግዳሮት በጥልቀት በማጥናት ለዘመናችን የአብነት ትምህርት ቤቶች አማራጭ የሌላቸው የእውቀትና የምግባር መገኛ ከመሆን በተጨማሪ ለሃገር እድገት ያላቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑን ለማሳየት ሊጠቅም ይችላል።

4. በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ተጨማሪ ጥናት ማድረግ ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች እንደመነሻ ተዛማጅ ጥናት ያገለግላል።

## 2. የጥናቱ ዘዴዎች (Research methodology)

### 2.1.የጥናቱ አቀራረብ ዘዴ (Research approach)

በዚህ ጥናት አይነታዊ የጥናት አቀራረብ ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል። ዘዴው የተጠኝዎችን ልምድና ገጠመኝ ከራሳቸዉ እይታ ተነስተዉ ሁኔታዎች ባሉበት አዉድ ስለሚገልጡ ለተመራማሪው ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። በዚህ ምክንያት በአብነት ተማሪዎችና በመምህራን አጠቃላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች ካሉበት ማኅበረ- ኢኮኖሚዊ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አገናንቶ ለማጥናት ስለሚያግዝ አይነታዊ የጥናት አቀራረብ ዘዴን መጠቀም ተችሏል። ይህ ጥናት በአብነት ትምህርት ቤቶች ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች መፈተሽን መሰረት ያደረገ ነዉ።

### 2.2. የጥናቱ ስልት

ዉስን ጥናት ስልት የአብነት ትምህርት ቤቶች ለመዳከማቸው ምክንያት የሆኑ ተግዳሮቶች ምን ምን እንደሆኑ የዳሰሰ ነዉ። ስልቱ ከአይነታዊ የጥናት ዘዴ አንዱ ሲሆን ይህን የመጠቀም ምክንያት የአጥኚውን አቅም በአንድ ርዕሰ ጉዳይና በተወሰነ ቦታ በጥልቀትና በስፋት በማጥናት ሰፊ ግንዛቤን ለማግኘት አግዟል። በዚህም ምክንያት በምስራቅ ጎጃም ሃገረ ስብከት ውስጥ ደብረማርቆስ እና ጎዛምን ወረዳ እንደ ማሳያ በመዉሰድ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አብነት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚታዩ ተግዳሮቶችን ዳሷል።

### 2.3. የንሞና አመራረጥ ዘዴ

ይህ ጥናት አላማ ተኮር የንሞና ሥልትን ተጠቅሟል። አላማ ተኮር የንሞና ስልትን የተጠቀመበት ምክንያት በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተሻለ መረጃ ያላቸዉ ተሳታፊዎችን በመረጃ ሰጭነት ዝርዝር ዉስጥ ለማካተት ነዉ። ስለዚህ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተሻለ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ተጠኚዎችን

በመለየት እዉነተኛ መረጃን መሰብሰብ ተችሏል። መረጃዎች እንደ አይነታቸዉና ጥልቀታቸዉ መጠን ለመሰብሰብ ተከታታይ የሆኑ ቃለ መጠይቆች እና ምልከታዎች ተደርገዋል። የጥናቱ ተሳታፊዎችን በፍላጎታቸዉና በችሎታቸዉ መሰረት በአላማ ተኮር የንሞና ስልት ተመርጠዋል። በተጨማሪ ከምስራቅ ጎጃም ሀገረ ስብከት ውስጥ በደብረማርቆስ እና በጎዛምን ወረዳ አላማ ተኮር በሆነ ስልት ገዳመ አስቄጠስ ተክለሃይማኖት አንድነት ገዳም (የቅኔ)፤ እንድማጣ ገነተ እየሱስ (የቅኔ)፤ መንበረ ስብሃት ቅድስት ስላሴ (የቅኔና የአቋቋም)፤ ግምጃ ቤት ኪዳነ ምህረት (አጫብር)፤ ጥሑመልሳን ወይንማ ማርያም (የዜማ)፤ የዛንግራ ቅዱስ ሚካኤል (የዜማ) ፤የደረባን ቅዱስ ሚካኤል (የዜማ) እና ሌሎች ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል። ምክንያቱም በነበረው ቅድመ መረጃ እና ከሃገረ ስብከት መምሪያ ሃላፊዎች ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ መሰረት ጥንታዊ እና ከፊደል እስከ ማስመስከሪያ የአብነት ትምህርት ቤቶች የሚገኙባቸዉ ቦታዎች ስለሆኑ ነዉ።

በጥናቱ የተሳተፉ ሰዎች በጉዳዩ ዙሪያ ጥልቅ እውቀት፣ መረጃና ቀረቤታ አላቸዉ ተብለው የሚገመቱ በጥናቱ መረጃ ሰጭ ዝርዝር ውስጥ ተካተዋል። በዚህም መሰረት ከሀገረስብከት ሀላፊዎች 5፤ ከአብነት ተማሪዎች (በየትኛዉም ደረጃ የሚገኙ) 8፤ ከመምህራን ከአስሩም ጉባኤያት (ከብሉይ፣ ከሀዲስ፣ ከሊቃውንት፣ ከመነኮሳት) ከዜማ፣ ከቅኔ፣ ከንባብ ወዘተ. ትምህርት ቤቶች 10፣ እና ከምእመኑ 20 ሰዎች ተመርጠዋል።

**2.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች**

የዚህን ጥናት ዓላማ ለማሳካት ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን መጠቀም ተችሏል። የሚከተሉት ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል፡-

**ሀ. ምልከታ**

ቦታው ድረስ በአካል በመገኘት በኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ መምህራን ሲያስተምሩ፤ደቀ መዛሙርት ሲማሩ፤ የመማሪያ እና የማደሪያ ቦታዎች፤ የሚማሩባቸውን ቁሳቁሶች፤ የመሰረታዊ ፍላጎት አቅርቦቶችን፤ የመሰረተ ልማት (ውሀ፣መብራት ሌሎችም አቅርቦቶችን) እና የተማሪ አያያዛቸውን፤ ወዘተ. ለማየት ተሞክሯል። ኢ-ተሳትዊ ምልከታ መጠቀም የተፈለገበት ምክንያት የሚሰበሰበው መረጃ የተመራማሪውን ቀጥተኛ ተሳትፎ ስለማይጠይቅ ነው። በምልከታ መረጃው ሲሰበሰብ አስፈላጊ የሆኑ ልዩ ልዩ መሳሪያዎች መቅረጸ ድምጽ፣ ምስል እና ድምጽ መቅረጫ መሳሪያ፣ ማስታወሻ ደብተር ወዘተ. አገልግሎት ላይ ውለዋል።

**ለ. ቃለ መጠይቅ**

ቃለ መጠይቅ በምልከታ ያልተገኙ መረጃዎችን ለማሟላት አስፈላጊ የመረጃ

መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው፡፡ በመሆኑም በከፊል የተደራጀ የመጠይቅ አይነትን በመጠቀም ለመምህራን፣ ለተማሪዎች፣ ለወላጆች እና ለሀገረ ስብከት ቢሮ ኃላፊዎች ስለ አብነት ተማሪዎች፣ ትምህርቱ እና ስለ አብነት ትምህርት ቤቶች እና አጠቃላይ መረጃዎችን በተመለከተ መጠይቅ ተደርጓል፡፡

**ሐ. የቡድን ተኮር ውይይት**

በቃለ መጠይቅና በምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለማመሳከር (triangulate) ለማድረግ የቡድን ተኮር ውይይት በየአብነት ትምህርት ማዕከላት ላይ አንድ አንድ ተዘጋጅተዋል፡፡ እያንዳንዱ ቡድን ስምንት ስምንት ተሳታፊዎችን ያቀፈ በአጠቃላይ ሰባት የቡድን ተኮር ውይቶች የሚካሄድ ሲሆን ይህም በግል ቃለ መጠይቅ ወቅት በደንብ ያልተብራሩ ሃሳቦችን በቡድን ዉይይት ወቅት እንዲዳብሩ እና ግልጽ እንዲሆኑ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

### 2.6. የጥናቱ ትክክለኛነትና ታማኒነት

የዚህን ጥናት ትክክለኛነትና ታማኒነትን ለማረጋገጥ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ተችሏል፡፡ ለምሳሌ ወካይ ንሞና እና ለርዕሰ ጉዳዩ ቅርብና ትክክለኛ ሰዎችን በመምረጥ ሃሳባቸዉን እንዲገልጡ ተደርጓል፡፡ በቃለ መጠይቅ በስፋት የተሰበሰቡ መረጃዎች ትክክለኛነትና ታማኝነታቸዉ ይበልጥ ለማረጋገጥ የሰነድ ማስረጃዎች በስፋት ተዳሰዋል፡፡

### 2.7. በጥናቱ ሊካተቱ የሚገባቸው ሥነ ምግባራት

እንደማንኛዉም ጥናትና ምርምር ይህ ጥናት የራሱ የሆነ የተከተላቸዉ የምርምር ሥነ ምግባራት አሉት፡፡ ከተለዩት የጥናት ቦታዎች መረጃ ለመሰብሰብ ሀገረ ስብከት አስተዳደር የድጋፍ ደብዳቤ መጠየቅ ፍቃድ በመቀበል፤ የጥናቱ ተሳታፊዎች ከተለዩ በኂላ ሥለ ጥናቱ ዋና ዓላማ በግልጽ በማብራራት ለሚጠየቁት ጥያቄ ለመመለስ ይረዳቸው ዘንድ ገለፃ ተደርጓል፡ ፡ በጥናቱ ሂደት ውስጥ በሰነድ ዳሰሳነት የገቡ መጻሕፍት በሙሉ እውቅና በመስጠት በዋቢ መጻሕፍት ላይ በዝርዝር ተጽፈዋል፡፡

## 3. የመረጃ ትንተና

### 3.1. የአብነት ትምህርት ቤቶች መዳከም፤

ከተለያዩ መረጃ አቀባዮች የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የአብነት ትምህርት ቤቶች ለመዳከማቸው እንደምክንያት የተገለጹት መሰረታዊ ፍላጎቶች አለመሟላት፣የተሻለ የስራ አማራጭ መፈለግ፣የጤና ችግሮች መኖር፣ የዘመናዊ ትምህርት ፍላጎት መኖር በዋናነት ይጠቀሳል፡፡

#### 3.1.1. የመሰረታዊ ፍላጎቶች አለመሟላት

በደብረማርቆስና አካባቢው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን የአብነት ተማሪዎች የተለያዩ የመሰረታዊ ፍላጎት ችግሮች

አሉባቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የምግብ፣ የመጠለያና የአልባሳት ፍላጎቶች እንዳልተሟሉላቸው መረጃ አቀባዮች ይጠቁማሉ፡፡ በተለይ ደግሞ ረሀቡ እጅግ በጣም እንደሚጠናባቸው ተማሪ ባንተላይ ቢምረው ቃለ መጠይቅ (15/3/2014 ዓ.ም) ሲገልጹ፡- ‹‹ረሀቡ ሲጠናብኝ የእናትና አባቴ ቤት ይመጣብኛል፡፡ ትቼ እንዳልሄድ ትምህርቴ ያስጨንቀኛል፡፡ግን ደግሞ ምእመኑ ካልዘከረን ረሀቡ ከጠናብን ትምህርቱን መቀጠላችን ችግር ነው፡፡ እንዴት እንደምናደርግ አናውቅም›› ይላሉ፡፡ በተጨማሪ ተማሪ በልስቲ ቃለ መጠይቅ (15/3/2014 ዓ.ም)‹‹እኛ ብዙ ችግሮች ናቸው ያሉብን ምግብ ፈልገን ካገኘን አገኘን ካላገኘን ደግሞ እንዳለ ሳንበላ እናድራለን፤ ምኝታው፣ልብሱ አንዳንድ መጽሀፍት አናገኝም፡፡ ችግሩ ብዙ ነው፡፡ የሚያግዝ የለም፡፡ እኛ ይህን ሁሉ ተቋቁመን አለን፡፡ ብዙዎቹ ጓደኞቻችን ግን ትተው ሂደዋል›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

ከላይ ካሉት ሃሳቦች መገንዘብ የሚቻለው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን የአብነት ተማሪዎች ትምህርታቸውን በመከታተል ሂደት ውስጥ ውጤታማ የማያደርጉ በርካታ ምክንያቶች እንዳሉባቸው አስረደተዋል፡፡እነዚህ ጉዳዮች መኖራቸው፤ለተማሪውና መምህራኑ መመናመን ምክንያት ሆኗል፡፡

### 3.1.2. የተሻለ የስራ አማራጭ መፈለግ

ምንም እንኳ ተማሪዎቹ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሥራ ሊያገኙ እንደሚችሉ ቢገነዘቡም፤ትምህርት የሚሰጥበት ጊዜ እረጅም መሆኑ፤ የክፍያ መጠኑ ማነሱ ለአብነት ትምህርት ቤቱ ተግዳሮቶች እንደሆኑ መረጃ አቀባዮች ያስረዳሉ፡፡መምህር ሰሎሞን ቡድን ተኮር ውይይት (27/4/2014 ዓ.ም) አንድ ተማሪ የመጨረሻውን የትምህርት ጣሪያ ለመድረስ ለምሳሌ መጽሃፍት (ሃዲስ ኪዳን፣ብሉይ ኪዳን፣መጽሀፈ መነኮሳት፣መጽሀፈ ሊቃውንት) እነዚህን ሁል ልማር ቢል እስከ 20 አመት ይወስዳል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ብዙ ችግሮች ስለሚኖሩ አማራጭ ስራዎችን ወደመፈለግ ይሄዳሉ፡፡ ሌላው ለረጅም አመት ተምረው ለቤተክርስትያን አገልግሎት ሲቀጠሩ የሚያገኙት ከፍተኛ ክፍያ ከተማ ላይ ከፍተኛው 8000 ሺብር ነው፡፡ ዝቅተኛ ካልን ደግሞ ሳይከፈለው የሚያገለግል አለ፡፡ 2000 ሺ ብር እየተከፈለው የሚያገለግል አለ፡፡ ከዚህ ሃሳብ ጋር በተያያዘ መምህር አእምሮ ቃለ መጠይቅ (12/04/2014) ክፍያው በጣም ይጎዳል፡፡ ገጠር እኮ ብር አይከፈልም በደብሩ ያለው ምእመን አንዳንድ ሳህን እህል እያወጣ ለአመት ይሰጣል፡፡ ያችን ቆጥበን እንበላለን፡፡ ይህ ከሌላው ጋር ሲወዳደር ወቅቱን ያላገናዘበ እጅግ በጣም የወረደ መሆኑ ለመምህራኑም ሆነ ለተማሪውም መመናመን ምክንያት ሆኗል፡፡ ስለዚህ ሀገረ ስብከቱ የመማሪያና ማስተማሪያ

መጻሕፍት፣የመምህራን ደሞዝ፣የመኖሪያ ቤት እና ሌሎችንም ማሟላት ቢችል ጥሩ ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ሃሳቦች የአብነት ትምህርት ቤት ተማሪዎችና መምህራን ለአገልግሎት የሚከፈላቸው ክፍያ እጅግ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ራሳቸውን ለማቆየት ካላቸው ፍላጎት የተነሳ የተሻለ ክፍያ ወደላቸው የስራ አማራጮች ይፈልሳሉ፡፡ይህ ደግሞ ለአብነት ትምህርት መዳከም እንደ ምክንያት ሊጠቀስ ችሏል፡፡

**3.1.3. የጤና ችግር መኖር**

በአብነት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎችና መምህራን ካለባቸው የመኖሪያ ቦታ ምቹ አለመሆን፣በቂና ጥራት ያለው መጸዳጃ ቤት አለመኖር፣ የምግብ እጥረትና ሌሎችም መከሰት ተማሪዎችን ለጤና ችግር አጋልጧቸዋል፡፡ ይህን በተመለከተ በምልከታ (23/04/2014) የተረጋገጠው፡- በአብነት ትምህርት ቤቱ ውስጥ በቂ የምግብ አቅርቦት አለመኖሩ፤የመጸዳጃ ቤት እጥረትና የንጽህና ችግር መኖሩ፤መኖሪያ ቤቱ የተስተካከለና ምቹ አለመሆኑ (ብርድና ዝናብ እንዲሁም ለጸሃይ መጋለጡ)፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የብርድ በሽታ፣ ኮሌራ፣አስም፣ ቲቪ የመሳሰሉት በሽታዎች አጥቅቷቸው ተማሪዎችን ተመልክተናል፡፡

መምህር ብርሃኔ ቃለ መጠይቅ (24/05/2014) ‹‹ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን በበሽታ ሲጠቁ የህክምና የሚያገኙበት እድል የለም፡፡ በዚህ ምክንያት ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው ተፈናቅለዋል›› በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከላይ የተገለጹት ምክንያቶች በትምህርቱ ላይ ተጽኖ በማሳደራቸውና ተማሪው እየተመናመነ በመሄዱ አሁን ላይ የአብነት ትምህርቱ ተዳክሟል፡፡

**3.1.4. የዘመናዊ ትምህርት ፍላጎት መኖር**

ማህበረሰቡ ዘመናዊ ትምህርት ራስን ለመለወጥና ለማሻሻል መሰረታዊ እንደሆነ ይገነዘባል፡፡ ካሉት የመለወጫ መንገዶች ውስጥ ትምህርትን በመምረጥ ልጆቹን ወደዘመናዊ ትምህርት ቤት ያስገባል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ዘመናዊ ትምህርት ተምሮ የተሻለ ደረጃ መድረስና ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻል በተጨባጭ የተረጋገጠ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ በመሆኑም ወላጆች የተሻለውን በመምረጥ ልጆቻቸውን ወደአብነት ትምህርት ቤት አይልኩም፡፡ ይህን በተመለከተ መምህር ተቋም(12/05/2014)‹‹ ምእመኑ ልጆቹን ወደ አብነት ትምህርት ቤት አይልክም፡፡ ምክንያቱም እዚህ መጠው ሲማሩ ሁሉን ጠንቅቀው ለማወቅ ከ20 እና ከ30 አመት በላይ ነው፡፡ ይህን ተምረው ሲጨርሱ ተቀጥረው የሚያገኙት ገቢ እዚህ ግባ አይባልም፡፡ ዘመናዊው ደሞ አመቱም እንደሀይማኖቱ ትምህርት ረጅም ጊዜ አይፈጅም ሲቀጠሩም ደሞዙ ጠቀም ያለ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የአብነት ትምህርት ቤቱ ተማሪም ተተኪ መምህርም አጧል›› በማለት ይገልጻሉ፡፡ በዘመናዊውና በአብነት

ትምህርቱ መካከል ያለው የጥቅም ልዩነት በአብነት ትምህርቱ ላይ አሉታዊ ተጽኖ አሳድሯል፡፡ በዚህ ምክንያት ምእመኑ ልጆቹን ወደዘመናዊ ትምህርት በመላክ ያስተምራል፡፡

## 3.2. የአብነት ትምህርት ቤቶች በመዳከማቸው ምክንያት የተጋረጡ ተግዳሮቶች

በመጀመሪያው የትንተና ክፍል ለማየት እንደተሞከረው የአብነት ትምህርት ቤቶች በተለያዩ ምክንያቶች ተማሪዎችና መምህራን ከሀይማኖታዊ ተቋማቸው እየወጡ ሂደዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በማህበረሰቡና በሀገር ላይ የተለያዩ ተግዳሮቶች ይስተዋላሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የተዘጉ የአብያተ ክርስቲያን ቁጥር፤የተለያዩ ቅርሶች መጥፋት፤ተማሪ የሌላቸው የትምህርት አይነቶች መኖር መጨመር፤ ማህበረሰቡ ሃይማኖታዊ አገልግሎት አለማግኘት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

### 3.2.1. የአብያተ ክርስቲያን ቁጥር ባለበት መቆም፤

በተማሪዎች እና በመምህራን መመናመን ምክንያት በተለያዩ አጥቢያዎች ያሉ ቤተ ክርስቲያን ባሉበት ከመቀጠል ውጭ የምእመኑ ቁጥር ሲጨምር አዲስ ቤተክርስቲያን መስራት አልተቻለም፡፡ ምክንያቱም አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ካህናት ቁጥር እየተመናመነ መምጣቱ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ ደርብ ተፈሪ (ቃለ መጠይቅ 23/03/2014 ዓ.ም) ‹‹አሁን ቤተክርስቲያን የሚገነባው በከተማ አካባቢ እንጅ ዙሪያውን ባሉት የገጠር አካባቢዎች ቀርቷል፡፡ ቀደም ተማሪውም መምህሩም ስላልተመናመነ ቤተክርስቲያ በየአካባቢው ይሰራ ነበር፡፡ አሁን ግን ቁጥሩ ባለበት ነው፡፡ በኛ ዙሪያ ቤተክርስቲያ አገልግሎት መስጠት እያቆሙ ነው፡፡ ስለዚህ ሀገረስብከቱ የአብነት ተማሪ ቁጥር መጨመር ላይ ይስራ ››በማለት ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪ አቶ ምስጋናው ላቂ ቡድን ተኮር ውይይት (27/04/2014 ዓ.ም) ‹‹አብያተ ክርስቲያናቱ ባሉበት እንዳሉ ናቸው፡፡ አዲስ ቤተክርስቲያን እየተገነባ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ያፈራነው፣ የተካነው፣ ዲያቆን ያደረግነው፣ካህን ያደረግነው ተተኪ የለም፡፡ በዚህ ምክንያት የአብያተ ክርስቲያኑ ቁጥር ባለበት ነው›› በማለት የላይኛውን ሃሳብ ያረጋግጣሉ፡፡ ከሀሳቡ መረዳት የሚቻለው የአብነት ተማሪዎችና መምህራን በመመናመናቸው ምክንያት፤በየአጥቢያው ቤተክርስቲያን የመገንባት እድል የለም፡፡

### 3.2.2. የተለያዩ ቅርሶች መጥፋት

የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖት ህልውና የሚጠበቀው ህጉን፣ስርዓቱንና ዶግማውን ጠንቅቀው የሚያውቁ በአብነት ትምህርት ቤት ያለፉ ተማሪዎችና መምህራን ያስፈልጓታል፡፡ ነገር ግን አሁን ላይ የሃይማኖት አስተምህሮውን የተገነዘበ አገልጋይ አለመኖሩ አብያተ ክርስቲያናቱን ሀብት ሲመዘብርና ሲዘረፍ ይስተዋላል፡፡ መርጌታ የትዋለ (ቃለ መጠይቅ

27/05/2014) ‹‹ሰው ሲጠፋ የሚያውቀውም የማያውቀውም አገልጋይ ሆኖ እየገባ የሚዘረፈው ሃብትና ቅርስ ብዙ ነው። ለዚህ ምክንያቱ የተማረ ለሀይማኖቱ ያደረ ሰው መጥፋቱ ነው›› በማለት ያስረዳሉ። የአብነት ትምህርት የተማረ በቂ የሆነ የሰው ሃይል አለመኖሩና ሀይማኖታዊ እውቀት የሌለው ሰው መግባቱ ቅርሶችን በቀላሉ ለዘረፋ ሲዳርጋቸው ይስተዋላል። ትላልቅ መጽሀፍት፣ መስቀሎች ይሰረቃሉ። ይህ ደግሞ ጉዳቱ ከማህበረሰብ ባለፈ በሀገር ላይ ጭምር ነው።

### 3.2.3. ተማሪ የሌላቸው የትምህርት አይነቶች መኖር መጨመር፤

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በሚሰጠው የአብነት ትምህርት ውስጥ የሚጠቃለሉ የተለያዩ የትምህርት አይነቶች አሉ። እነዚህም አቋቋም ቤት፣ድጓ ቤት፣ቅዳሴ ቤት፣ዜማ ቤት፣ቅኔ ቤት፣መጽሀፍት ቤት ናቸው። ከእነዚህ የትምህርት አይነቶች ውስጥ ተማሪያቸው እየተመናመነ የመጣና ፈጽሞ የሌላቸው ትምህርቶች እንዳሉ በምልከታ (23/05/2014) ተረጋግጧል። ከነዚህ ውስጥ በጣም ጥቂት ተማሪ ያላቸው የትምህርት አይነቶች በኢትዮጵያ ውስጥ በምስራቅ ጎጃም በደብረማርቆስ ከተማ ኪዳነምህረት ቤተክርስቲያን ብቻ የሚሰጠው የአጫብር ድጓ 5 ተማሪ እና 1 መምህር ብቻ እንዳለው በቦታው በመገኘት ለማስተዋል ተችሏል። ለዚህ ምክንያቱ ትምህርቱ አድካሚ መሆኑን ተማሪዎች ይገልጻሉ። አሁን ላይ ሙሉ በሙሉ የጠፋ ወይም ተማሪ የሌለው አቡሻህር ነው። መምህር አዕምሮ ቃለ መጠይቅ (27/05/2014) አቡሽሀር በተለያዩ ተጽኖዎች አሁን ላይ ጠፍቷል። ምክንያቱም ትምህርቱ ከባድ ነው። አንዳንዶች ከጥንቆልና ጋርም ያያይዙታል። በማለት ያወሳሉ። ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱት የትምህርት አይነቶች አሁን ላይ የጠፉና በመጥፋት ላይ ያሉ እንደሆኑ መረዳት ተችሏል።

### 3.2.4. ምእመኑ ሀይማኖታዊ አገልግሎት አለማግኘት

የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምእመናን የሀይማኖቱ ስርዓት በሚፈቅደው መሰረት ከቤተ እምነታቸው አገልግሎት ያገኛሉ። ከእነዚህ ውስጥ የቅዳሴ፣ የክርስት፣የፍትሀት፣ የንስሀ፣ የሰርግና ሌሎችም ይጠቀሳሉ። በምልከታ (23/05/2014) እንደተስተዋለው እነዚህ ተግባራት በካህናትና ዲቆናት የሚከወኑ ቢሆኑም፤በቂ የሆነ መምህርና ተማሪ ባለመፈራቱ የተነሳ በገጠር አጥቢያዎች ማለትም እንዶዳን ኪዳነምህረትና ቸርተከል አማኑኤል አገልግሎት የሚሰጠው የክርስትና፣ የፍትሃት፣የንስሀ አገልግሎት የሚሰጡ ባለመኖራቸው ምእመኑ ወደሌላ አጥቢያ በመሄድ ይገለገላል። የቅዳሴ አገልግሎት ደግሞ በወር አንድ ጊዜ እና አልፎ አልፎ በየሁለት ሳምንቱ አገልጋይ ካህን በማስመጣት ያስቀድሳሉ።

## ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት አጠቃላይ ዓላማ በደብረማርቆስ እና ጎዛምና ወረዳ አካባቢ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስተያን በአብነት ትምህርት ቤት የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች መርምሮ ማሳየት ነው፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ መረጃዎች ተሰብስበው በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ በመሆኑም፤ጥናቱ በመረጃ ትንተናው ሁለት ውጤቶች አመላክቷል፡፡ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የአብነት ትምህርት ቤት ዘመናዊዉ ትምህርትን ኢትዮጵያ ከመጀመሯ ከብዙ ሺህ አመታት አስቀድሞ ፊደል ቀርጻ፣ የራሷን ቋንቋ ፈጥራ፣ ብራና ዳምጣ ቀለም በጥብጣ  በአካባቢዉ የሚገኙ በርካታ ህጻናት ያለብዙ ድካም መሰረታዊ የፊደል፣ የኃይማኖት፣የስነምግባር እና የስነ ፍጥረት ትምህርትን የሚማሩበት ቀዳሚዉ ትምህርት ቤት ነዉ፡፡ ይሁን እንጅ አሁን ላይ የአብነት ትምህርት ቤቶች በከፍተኛ ሁኔታ እየተዳከሙ መጥተዋል፡፡በመሆኑም በደብረማርቆስ እና ጎዛምና ወረዳ አካባቢ ያሉ የአብነት ትምህርት ቤቶች ለመዳከም ምክንያቶች መሰረታዊ ፍላጎቶች አለመሟላት፣ የአብነት ተማሪዎች የተሻለ የስራ አማራጭ መፈለግ፣የጤና ችግሮች መኖር እና የዘመናዊ ትምህርት ፍላጎት በወላጆችና በተማሪዎች እየጨመረ መምጣት ትልቅ ምክንያት ሆኗል፡፡ ሁለተኛው፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚታየው የአብነት ትምህርት ቤቶች በመዳከማቸው ምክንያት በሀገርም ሆነ በማህበረሰቡ ላይ የተጋረጡ ልዩ ልዩ ተግዳሮቶች ሲሆኑ ከእነዚህውስጥ የቤተክርስቲያን ቁጥር ባለበት መቆም፤የተለያዩ ቅርሶች መጥፋት፤ተማሪ የሌላቸው የትምህርት አይነቶች መጨመር ፤ማህበረሰቡ ሃይማኖታዊ አገልግሎት (ቅዳሴ፣ ክርስትና፣ፍተሃት፣ንስሀ እና ሌሎች ጸሎቶችን) አለማግኘት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

**የመፍትሄ ሀሳቦች**

ከጥናቱ ውጤት በመነሳት የሚከተሉት የይሁንታ ሃሳቦች ማስቀመጥ ተችሏል፡፡

- የትምህርት ቁሳቁስ እጥረት፣ በቂ የመማርያና የመኖሪያ ቦታ አለመኖር፣ የህክምና አገልግሎት አለመኖር ወዘተ. በአብነት ትምርት ቤቶች ዘንድ በስፋት የሚታዩ ጉድለቶች በመሆናቸዉ የምስራቅ ጎጃም ቤተክህነት አስተዳደር ትኩረት ቢሰጠው፡፡
- የአብነት ትምህርት ቤት የትውልዱን ስነምግባር ከመገንባት እና ብቁ ዜጋ ከማፍራት አንጻር አስተዋጽኦ ስላለው የመንግስት አስተዳደር አካላት፣ ማህበረሰቡ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ባለሀብቶች ወዘተ. የየድርሻቸውን ቢወጡ ፡፡
- የአብነት ተማሪዎችን ለብዙ ዘመናት ምእመኑ ስንቅ እየቋጠረና እየተንከባከበ እንደልጁ አድርጎ የሚያስፈልጋቸዉን እርዳታ በማድረግ አቆይቷል፡፡ ስለዚህ የተማሪዉና የምእመኑን ግንኙነት አጠናክሮ

የማስቀጠያ ስልቶችን ወዘተ. በተመለከተ ብዙም አልተጠናም። ስለሆነም በዚህ ጉዳይ ጥናትና ምርምር ቢደረግ መልካም ነው

## ዋቢ መጽሐፍት


መሸሻ አለሽኝ። (2011) ። በእንተ ስመ ለማርያም። ጥንታዊዉ የኢትዮጵያ ትምህርት ይዘቱ፣ ሥርዓቱና ሕይወቱ። ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ. የግ.ማኅበር።

ባህሩ ዘዉዴ። (1999) ። ዘመናዊ ኢትዮጵያ ታሪክ ከ1948-1983 ዓም፤2ኛ እትም፣አዲስ አበባ። (1994). የዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ ከ1948-1966 ዓ.ም 2ኛ እትም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ።

ገነት ከበደ። (ዓመተ ምህረቱ ያልተጠቀሰ)። የአብነት ትምህርት ቤቶች የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትናንት፤ ዛሬና ነገ (The Ethiopian church past, present and future)።

Ashenafi, Kassahun. (2011). Ye'kolo-temari: Children's Perspectives on Education, Mobility, Social Life and Livelihood in the Ethiopian Orthodox Church (EOC) Traditional School in Dangila'. 2011 እኤአ. MA thesis. Norwegian Center for Child Research.

Aweke, Shishigu. (2015). Foundation of Curriculum in Ethiopia: Historical, Philosophical, Psychological and Sociological Perspectives.

Ayenachew, A. Woldegiyorgis (2017), (nd). The Ethiopian Traditional Education: Philosophical foundations and reformist movements in Medieval Period. Lynch School of Education. EDUCAZIONE. Giornale di pedagogia critica, VI, 2 pp. 7-29. ISSN 2280-7837 © 2017 Editoriale Anicia, Roma, Italia. DOI: 10.14668/Educaz_6202.

Chaillot, C. (2002). The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church Tradition - a Brief Introduction to its Life and Spirituality. Inter-Orthodox Dialogue, Paris

Enbakom, Kalewold.(1974). Traditional Ethiopian Chllrch School. New York: Columbia University press.

Hilegebrel, Melak.(1994). SymposiulII on The /lIll1re o/religiolls sllidies in Elhiopia and Erill"ea. volume V. Addis Ababa Ubiversity.

Jangawe, M. (2007). Challenges and opportunities in the protection and preservation of indigenous knowledge in Africa. International Review of Information Ethics 7:

Mezmur,Tsegaye.(2011). Traditional Education of the Ethiopian Orthodox Church and Its Potential for Tourism Development (1975-present). Addis Ababa University.

Munjeri, D. (2000). Intangible heritage in Africa: could it be a case of 'much ado about nothing? ICOMOS Newsletter.